# አላማህ ምንድነው?

# 2010 አለም አቀፍ. ተበረታታ ፣ ተሳተፍ

**ጁን 6 2010 ለመላው ክርስትያኖች ከአለም ዙሪያ የእግዚአብሔርን አላማ ጥሪ በደማቅ መልኩ ለማክበር ይጋብዛችኋል፡፡**

***ማንም ሁን የትም ኑር፤ ይችህ ቀን ከእግ/ር በእምነት ለተቀበልናቸው ማናቸውም ነገሮች ምስጋና የምናቀርብበትና ራሳችንን ለክርስቶስ አስገዝተን ምስክር መሆናችንን በጋራ የምናሳይበት ቀን ነው!***

## 1910 ምን ነበር?

በአለም ዙሪያ ካሉ የተለያዩ ቤተ ክርስትያኖች የተወጣጡ በርካታ ክርስትያኖች ቤተክርስትያን በአለም ላይ ስላላት አላማ የተወያዩበት ታላቁ የአለም የሚሽነሪዎች ኮንፍራንስ በ ኢዲንበርግ በ 1910 እ.ኤ.አ ከተዳሄደ 100 ዓመት አስቆጥሯል፡፡ በዚያ ኮንፈራነስ ላይ የተሳተፉት አብዛኞቹ ነጮች፣ ምዕራባዊያን እና ወንዶች ነበሩ፤ ቢሆንም ታሪካዊና ፈር ቀዳጅ ጊዜ ነበር፡፡ ተሳታፊዎቹ ከቀኝ ግዛት አስተሳሰብ ተላቀው አዲስና እያደጉ ያሉ ራሳቸውን የቻሉ ራሳቸውን የሚያስተዳድሩ በአለም ዙሪያ ያሉ ቤተ/ክርስትያኖችን በመቀበል ተስማምተዋል፡፡

### ውጤቱ ምን ነበር?

ከዛን ጊዜ ጀምሮ ክርስትያኖች እንዴት አብሮ መስራትን ፣ እንዴት የእግ/ር የፍቅሩን ዜና መጋራት እና እንዴት የክርስቶስ ምስክር መሆን እንደሚቻል በሚገባ ተምረዋል፡፡ ይህንንም የሆነው በተለያዩ መንገዶች ሲሆን ለምሳሌ፡ ድሆችን በመርዳት ፣ ፍትህን በማስከበር ፣ ዘረኝነትን በመዋጋት ፣ ለመግባባት በመስራት እንዲሁም አለምን በመንከባከብ ነው፡፡ ክርስትያኖች እርስ በእርስ በመግባባትና ከሌሎች እምነት ተከታዮች ጋር በመስራት ከላይ የተጠቀሱት በተለያየ መልክ እና ባህል እንዲተገብር አድርገዋል፡፡ ያለ 1910 ግፊት ይህ ሁሉ አስቸጋሪ ይሆን ነበር፡፡

### ምልከት ፣ ጥናት ፣ ተግባር

ካለፉት ጥቂት አመታት ጀምሮ አንድ ቡድን የ1910ን ተፅዕኖ እንዴት እንደሚለካና በአሁኑ ጊዜ የክርክትያኖችን አላማ የሚገዳደሩትን ነገሮች በማጥናት ላይ ነው፡፡ እንዲሁም የተለያዩ የጥናት ቡድኖች በአሁኑ የክርስትያኖች እምነት ተፈጥሮና ምንነት ጋር በተያያዙ ጉዳዮች እና እንዴት የ1910 ውልደት በተሻለ መልኩ በአለምና በኢዲንበርግ ማሳየት አንደሚቻል ጥናት እያደረጉ ይገኛሉ፡፡

### አለም አቀፍ እና አገር አቀፍ

የ1910 ኮንፍራንስ የተካሄደው በጥንታዊቷ ምዕራባዊ ከተማ ውስጥ ነው፡፡ ከ 100 ዓመት በኋላ ደግሞ በአሉ አለም አቀፍም፣ አገር አቀፍም ፣ እንዲሁም በተቻለ መጠን ሁሉን አሳታፊ እንዲሆን እንፈልጋለን፡፡ የዘመኑ ቴክኖሎጆዎችና ኢንተርኔት ይህ አንዲሳካ የተለያዩ መንገዶችን ከፍተዋል፡፡ የ2010 ፕሮጀክትን እግ/ርን አመታት ላሳለፈው አላማው ማመስገኛ እና ከፊታችን ያሉትን ተግዳሮቶች ለመቋቋም እንዲሁም ለማስቀረት እንደ አጋጣሚ የምትጠቀምበት/ሚበት ነው፡፡

**የሁለት መንገድ ስራ**

በ1910 ተነሳሽነቱ ከኢዲንበርግ ነበር የመጣው ፤ አሁን በ 2010 እኛ በአለም ላይ የምናከብረው በዓል ወደ ኢዲንበርግ መልዕክት ይልካል፡፡ በጁን 6 2010 እ.ኤ.አ ምልክት የሚሆን ተግባር ፣ ምስጋና የሚሰጥበትና ቃል የሚገባበት ስነስርዓት በኢዲንበርግ በ 14:00 GMT ይካሄዳል፡፡ በተመሳሳይ ሰዓት በተለያዩ የአለም ክፍል ያሉ ክርስትያን ማህበረሰብ የራሳቸውን በአል እንዲያከብሩ እናበረታታለን፡፡ በዚህ መልኩ የአለም በተክርስትያኖች ለአለም አቀፉ አላማ በአንድነት ቃል ሲገቡ ማየት አንፈልጋለን፡፡

**2010. አለም አቀፍ - በዚህ መልኩ መሳተፍ ትችላላችሁ!**

የራሳችሁን የአገር ውስጥ የአላማውን በአል በ ጁን 2010 በማዘጋጀት በአለም ላይ ያሉትን የክርስትያን ቡድኖችን ተቀላቀሉ፡፡ በዓሉን ከራሳችሁ ፕሮግራም ጋር በሚሄድ መልኩ በማንኛው ጊዜ ማዘጋጀት ትችላላችሁ ወይንም በ ጁን 6 ከሌሎች አከባሪዎች ጋር፡፡ አከባበሩ የሚከተሉትን ሊያካትት ይችላል፡

- በህብረት የሚደረግ መንፈሳዊ አምልኮ ጊዜ
- የወጣቶች ምሽት
- የድራማ ዝግጅት
- የጉብኝት ጊዜ
- የቤት ለቤት አከባበር

**የኛን አለም አቀፍ 2010 ሞዴል እንደ መሪ ተጠቀሙ**

አንድ ዝግጅት ለማዘጋጀት የማትችሉ ከሆነ ፤ አትጨነቁ ፤ ቀላል ሞዴልና ስለ ፕሮጀክቱ መረጃ ከ ዌብ ሳይታችን www.edinburgh2010.org ማግኘት ትችላላችሁ፡፡ ሞዴሉን በመጠቀም ከራሳችሁ ዘይቤ እና ባህል ጋር የሚሄድ አከባበር ማዘጋጀት ትችላላችሁ፡፡ በየሀገሩ የደስታ መግለጫ ፣ ምስጋና እና የአላማው ተገፐነትን እንደምናይ ተስፋ እናደርጋለን፡፡ ለእግ/ር ፍቅር ትልቅ ምስክርነት ይሆናል፡፡

**ምልክት አዘጋጅ**

እግ/ር በራሳችሁ አለም በአንተና በክርስትያኖች ላይ ያለውን አላማ ሊገልፅ የሚችል ቅርፅ ወይንም ምልክት ማዘጋጀት ትችላለህ? የእግ/ርን መገኘት የሚያሳይ አንድ ተራራ ቅርፅ ሊሆን ይችላል፣ ወይንም እድገትንና አዲስነትን የሚናገር የአንተ አገር ዛፍ ስሩና ቅርንጫፉም ሊሆን ይችላል፣ አልያም የእግ/ርን በህዝቡ ውስጥ ስላለው የመንፈሱ እንቅስቃሴ የሚያሳይ የባህር ላይ ነፀብራቅ ሊሆን ይችላል፡፡ አማራጮች ብዙ ናቸው፡፡ ምልክቱን በጋራ ልትሰሩት ትችላላችሁ፡፡ ወይንም በአርቲስት መጠቀም፣ በቤተ/ክርስትያን እና የእሁድ የህፃናት ክፍል ውስጥ ውድድር ማዘጋጀትም ይቻላል፡፡ መታወቂያ፣ ባንዲራ፣ ከነቴራ ወይንም የሚሰቀል ፅሁፍ ማዘጋጀት ይቻላል፡፡ የቤተ/ክርስትያን አርማም ሊሆን ይችላል፡፡ የተሠራውን ስራ በዌብ ሳይታችን www.edinburgh2010.org ልታስተላልፉ ትችላላችሁ፡፡ እኛም ከአለም ዙሪያ የተሠባሰቡትን ስዕሎች በላይብረሪ ውስጥ እናስቀምጠዋለን፡፡

**ከኛ ጋር ፀልዩ**

ሁሉን ባካተተ እና አንድነት በተሞላበት መልኩ እግ/ርን በዚህ ፀሎት እንድናመሰግን ኢዲንበርግ 2010 ይጠይቃል፡፡ እናንተም የራሳችሁን የፀሎት ርዕስ ፃፉትና ሌሎችም እንዲጠቀሙበት ኢጋሩን፡፡

የፀጋ አምላክ እግ/ር ሆይ
ፍቅርህ በአንተ አለም ላይ በብዛት ይፈሳል
ቀርበህ ህመማችንን ፈወስከ
ልባችንንም በተስፋ አነደድከ
አህንም ምስጋናን ለአንተ ስንሰጥ
አላማህንም ስናከብር
ስንስማማ ፣ ስንጠጋገንና ስንለዋወጥ
ከአንተ በሆነው አስገራሚ የፍቅር መንፈስ ሙላን
በክርስቶስ እየሱስ ስም
አሜን

**ይህን ታላቅ አለም አቀፍ በአል ጁን 6 2010 ተቀላቀሉ**

የኢዲንበርግ የሚሽነሪነት **በአል በጁን 6 2010** እለተ **እሁድ በ** 14:00 GMT **ላይ ይ**ከበራ**ል**:: የእናንተንም ዝግጅት **ለምን** በተመሳሳይ ጊዜ አታካሂዱም? በምስራቅ ላላችሁ የምሽት ዝግጅት ይሆናል ለምዕራብ ደግሞ የጠዋት፡፡ ለሌሎች ደግሞ የማይመች ሰዓት ስለሚሆን በሌላ በተመቻቹ ጊዜ አድርጉ፡፡ በየጊዜው በሚደረግ ፕሮግራም ውስጥም ይህንን የተለየ ፕሮግራም ማካተት ይቻላል፡፡ ኢዲንበርግ 2010 የተለያዩ ቡድኖችን እንዴት በኢንተርኔት በ ጁን 6 እንሚያገናኝ እየሰራ ነው፡፡ ለበለጠ መረጃ የመረጃ መረባችንን ተመልከቱ www.edinburgh2010.org

**በአሉን ወደ ተግባር ይለወጥ!**

- በምታደርጉት የራሳችሁ በአል ላይ በእግ/ር አላማ ላይ አንድ እርምጃ የሚያስኬድ ውጤት እንዴት ማምጣት እንደሚቻል አጥኑ፡፡ ትኩረቱ ምን ላይ መሆን አለበት;
- በተግባር እቅድ ላይ መስማማት ትችላላችሁ;
- በምስጋና ፕርግራሙ ላይ የምታገኙትን ውጤት ከሌሎች ጋር መጋራት ትችላላችሁ;
- በራሳችሁ ክልል ለሚመጡት አመታት ምን ራዕይ አላችሁ;
- ራዕዮን ለማሳደግ ምን አላማ አላችሁ;
- አለም ስትቀየር አንተ ልታደርግ ያሰብከው የተለየ ነገር አለ;
- ከሌሎች ክርስትያኖች ጋር ምን አብረህ ልትሰራ ትችላለህ ብቻህን ከምትሰራው ውጪ;

**የኢዲንበርግን 2010 ዌብ ሳይት ተጠቀሙ**

ራዕያችሁን፣ህልማችሁን እና የስራ አላማችሁን በዌብ ሳይታችን www.edinburgh2010.org አጋሩን፡፡ ሌሎችም አይተው በምትሰሩት ስራ ይበረታታሉ፡፡ስርዓቱን በ ጁን 6ም ሆነ መሌላ ጊዜ አቅዱት፤ ስራችሁን የሚያጠናክርና የሚያጎለብት የተለያዩ ሀሳቦችን ማግኘት ትችላላችሁ፡፡ ከዚህም አዲስ ጓደኝነት፤የስራ ባልደረባ እና ትስስር ሊፈጠር ይችላል፡፡ እግ/ር ለሁላችንም አስገራሚ ነገር አለው፡፡

**አረንጓዴ እንሁን**

የእግ/ር ፍጥረት በትልቅ አደጋ ላይ ነው ያሉት፤ እናም እኛ ሁላችን የአደገኛውን ጋዝ ልቀት በፍጥነት መቀነስ አለብን፡፡ በአረንጓዴ ጉዞ 2010 አለም አቀፍ በሚያደርገው ስራ ላይ የበለጠ መረጃ ለማግኘት ዌብ ሳይታችንን www.edinburgh2010.org ይጎብኙ፡፡

**በመጨረሻ...**

ኢዲንበርግ 2010 ሊሳካ የሚችለው ሁላችንም ስራችንን ስንሰራ ነው፡፡ እንደ እግ/ር ታላቅ ፍቅር ተጠሪዎች ተስፋንና ፈውስን በአለም ዙሪያ ላሉ የእግ/ር ሰዎች ማምጣት አለብን፡፡

**እነዚህ ድርጅቶች ኢዲንበርግ 2010ን ይደግፋሉ**

አፍሪካ ኢንዲፔንደንት ቸርችስ፣ አንጀሊካን ኮሚኒዮን፣ ኤሲያን ፔንቴኮስታል ሶሳይቲ፣ ባፕቲስት ዎርልድ አሊያንስ፣ ቸርች ኦፍ ስኮትላንድ፣ ቸርችስ ቱጌዘር ኢን ብሪቴን ኤንድ አየርላንድ፣ ካውንስል ኦፍ ዎርልድ ሚሽን፣ ኢንተርናሽናል አሶሲየሽን ፎር ሚሽን ስተዲስ፣ ኢንተርናሽናል ፌሎውሺፕ ኦፍ ኢቫንጀሊካል ስቱደንትስ፣ ላቲን አሜሪካን ቲዮሎጂካል ፌሎውሺፕ፣ ሉዛኔ ኮሚቴ ፎር ዎርልድ ኢቫንጀላይዜሽን፣ ሉተራን ዎርልድ ፌደሬሽን፣ ኦርቶዶክስ ቸርቸስ፣ ሮማን ካቶሊክ ቸርች፣ ሰቨንዝ ዴይ አድቬንቲስት ቸርች፣ ዎርልድ አሌያንስ ኦፍ ሪፎርምድ ቸርችስ፣ ዎርልድ ካውንስል ኦፍ ቸርችስ፣ ዎርልድ ኢቫንጀሊካል አሌያንስ፣ ዎርልድ ሜቶዲስት ካውንስል፣ ዎርልድ ስቱደንት ክርስትያን ፌዴሬሽን፡፡

***ያግኙንና ራዕዮን ያጋሩን***

ኢዲንበርግ 2010
ጃዝሚን አዳም
የኮሚውንሽን ሀላፊ
ኢሜል: jadam@cofscotland.org.uk
ዌብ ሳይት: www.edinburgh2010.org
በ እስካይፐ, ፌስቡክ እና ትዊተር ላይ ያገኙናል፡፡